# ጉዞ ወደ ነገዋ ኢትዮጵያ (ክፍል ፩)

አንዱ ዓለም ተፈራ   ሰኞ ታኅሳስ ፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ. ም. (21/12/2020)

በአገራችን የፖለቲካ መድረክ፤ የዘመናት ብሶት፣ የታፈነ ስሜት፣ ድህነት፣ ሥራ አጥነት፣ ተስፋ ማጣት፣ እኔ ብቻ ነኝ ትክክለኛ! ባይነት፣ እናውቅልሃለን ባይ ሥልጣን ፈላጊ ልሂቃን፣ በየደረጃው ራዕይ ያላቸው መሪዎች አለመገኘታቸውና መሪ ያጡ ተከታዮች ብዛት ተደበላልቆ፤ ትክክለኛ መንግሥትና ትክክለኛ ተፎካካሪዎች የሌሉበት የፖለቲካ መድረክ ነግሷል። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ፈልጎት ይሁን ተጭኖበት፣ የውጪ ኃይላት ቀምመውት ይሁን ሁኔታውን ተጠቅመውበት፣ ተፎካካሪዎች የፉክክሩን ሜዳ ስላልተረዱት ይሁን አካሂያዱን ስላላወቁበት፤ አሁን ያለው የፖለቲካ ሀቅ እግሩን አንሰራፍቶ መድረኩን ተቆጣጥሮታል፡፡ ከዚህ ወጥተን ወደ ትክክለኛው መንገድ መግባት አለብን። ትክክለኛው መንገድ የትኛው ነው? ትክክለኛነቱ በምን ሚዛን ተሰፈረ? እናስ እንዴት ይኬድበታል? ይህ ጽሑፍ፤ በዚህ ዙሪያ ያለውን ይፈትሻል።

በየዜና አውታሩ የሚተረከውን ዘግናኝ አረመኔያዊ የትሕነግ ተግባር ያልተከታተለና ይህ ያልሰቀጠጠው ይኖራል ብዬ አላምንም። ከታናሽ ወንድሜ ጋር በአገራችን ስላለው የፖለቲካ ሁኔታ ስንወያይ፤ እኔ በየዕለቱ የምሰማው ኢሰብዓዊ ጭካኔ እየሰቀጠጠኝ፤ የዜና አውታሮችን መከታተል ችላ ማለቴን ነገርኩት። እሱም፤ ለምን ይመስልሃል ይሄን የመሰለ አረመኔነት የታየበት? ለምንስ በአማራዎች ላይ ጠነከረ? ሲል ጠየቀኝ። ለምን? ለሚለው የሱ ጥያቄ፤ ከኪሴ አውጥቼ የምወረውረው መልስ አልነበረኝም። አንድና አንድ ሁለት ነው እንደሚለው የተማርኩት የሂሳብ ቀመር፤ ትክክለኛ የሆነ መልስ በቀላሉ የሚዘገን አልሆነልኝም። እናም ያለመልስ አለፍኩት። ከጨዋታችን በኋላ ግን፤ ክብደት ሠጥቼ አሰብኩበት። ለዚህ መልስ እንደ አገር የምናቀርበው ከሌለን፤ የምንሄደው ወደፊት ሳይሆን፤ ወደ ነበርንበት የሚመልሰንን እሽክርክሪት የሆነበት የዙሪያ ጥምጥም ጉዞ ነው። ስለ ትናንት እየተረከ ነገር ግን ከትናንት ያልተማረ፤ ዛሬን ትናንት አድርጎ ነገም ትናንት እንዲህ ነበር! የሚል ተራኪ ይሆናልና! አሁን መመርመር ያለባቸው ጉዳዮች፤ በጣም ባስደናቂ ሁኔታ የተካሄደው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር (ትሕነግ) ችንፈት፣ አሁን ያለው የአስተዳደር ሥርዓትና የተፈለገው ለውጥ፣ በተጨባጭ ያለው የፖለቲካው ሂደት ናቸው።

የትሕነግ ችንፈት የዚህ ጽሑፍ መነሻ ነው። ለወደፊቱ በታሪክ ብዙ ጥናት የሚደረግበት አስገራሚው የትሕነግ ጦር ጫሪነትና ያጭር ጊዜ መፈራገጥ፤ ለዚህ ጸሐፊ በጣም ግራ የሚያጋባ ሆኖበታል። በመጀመሪያ ደረጃ፤ የትሕነግ መሪዎች አዲስ አበባንና ሕጋዊውን መንገድ ንቀው መቀሌ ያለ አግባብ ሲሰባሰቡ፤ ራሳቸው ራሳቸውን ከጨዋታ ውጪ አደረጉ። ያን ማድረግ ብቻ አይደለም፤ በኢትዮጵያ በየመሥሪያ ቤቱ በኃላፊነት የሰገሰጓቸውን አባላቱን፤ ኃላፊነታቸውን ትተው ወደ መቀለ እንዲነጉዱ አዘዙ። እንደኔ ላለ ኢትዮጵያዊ፤ ይህ አንድም የራሳቸውን መንግሥት ለማወጅ መዘጋጀታቸው፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ፤ ወደ መውደቂያቸው ገደል ጥግ ተጠግተው ጦርነት ሊያውጁ መወሰናቸውን ነገረው። የትሕነግ አመራር በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ ያካሄደውን የጅ አዙር አረመኔ ተግባር፤ ደግሞ በትግራይ ውስጥ በሰፊው የዉጊያ ስልት አድርጎ ተጠቀመበት። እውነት ነው ብሎ ማመን ከበደ። በማያጠራጥር መንገድ በፎቶና በቪዲዮ፣ በቦታው ከነበሩ የዓይን እማኞችና ሄደው የዘገቡ ጋዜጠኞች ተረዳን። በሌላ በኩል ደግሞ፤ የወልቃይትና ጠገዴ፣ የጠለምትና ድብባሕር፣ የራያ ፋኖዎች፤ ከአማራ ልዩ ኃይል ጋር ለመከላከያው ሠራዊት ያደረጉትን ደራሽነትና ተጋድሎ ተረዳን። ከዚያም መከላከያ ሠራዊታችን በጨለማው ወቅት በደረሰበት ተንኮልና ቅንብር እጁን ሳይሠጥ ያደረገውን አገር ወዳድ ተጋድሎ ተገነዘብን። እውነትንና ቆራጥነትን ያነገበው ሠራዊታችን፣ የአማራ ልዩ ኃይልና ፋኖ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከትሕነግ ጥፍር አላቀቁት። ይህ በትሕነግና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የነበረው ሕግ የማስከበር ሂደት፤ የጥቂት ትሕነግ መሪዎችን የሥልጣን ጥማት አባዜ የሚመለከት ብቻ ሳይሆን፤ መሠረታዊ የሆነውን የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር የፖለቲካ ፍልስፍናና ተግባር፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ጋር ያፋጠጠ ነው። እናም የተቸነፈው፤ ትሕነግ ብቻ ሳይሆን፤ የትሕነግ የፖለቲካ ፍልስፍናና ተግባር ነው። የዚህ ፍልስፍና ማዕከላዊ አምዱ የትሕነግ ሕገ-መንግሥት ነው። በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ፤ የትሕነግን

ዘለዓለማዊ የበላይነት ጠባቂ አምዶች ተዘርግተዋል። መነሻውም ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳትሆን፤ የኢትዮጵያ ብሔርና ብሔረሰቦች ናት የሚለው ነው። ለምን ይሄ እንደተደረገ መግለጡ የዚህ ጽሑፍ ትኩረት አይደለም። ሊሰመርበት የሚገባው ግን፤ በዚህ ስሌት ግለሰብ ኢትዮጵያዊ አለመኖሩ ነው። በዚህ ላይ እናተኩር።

የአንድ ግለሰብ ኢትዮጵያዊነትና የቡድን ኢትዮጵያዊነት ባንድነት ሊኖሩ አይችሉም። እዚህ ላይ ነው ኢትዮጵያዊነትና የትሕነግ ፍልስፍና መስመራቸው የሚለያየው። የትሕነግ ኢትዮጵያዊነት መሠረታዊ ግቡ፤ ኢትዮጵያዊያንን በየጎራቸው ከፋፍሎ፤ የየራሳቸውን ማንነት በማስታጠቅ፤ ልዩነታቸውን መታወቂያቸው በማድረግ፤ ለወደፊቱ የተበጣጠሰች ኢትዮጵያን ማዘጋጀት ነበር። ይህ ርዕዩት ከትክክለኛ አገር ወዳድነት ኢትዮጵያዊነት ጋር ይጋጫል። አንድ ግለሰብ፤ የራሱ ወይንም የራሷ የሆነ ነፃ አመለካከት ኖሯት በአገራችን የፖለቲካ ሂደት ተሳትፎ ካላደረገች፤ ሰብዓዊ ማንነቷን ተነፈገች ማለት ነው። እንዲህ ያለ ራሱን ችሎ የሚያስብ ግለሰብ በኢትዮጵያ እንዳይኖር ነበር የትሕነግ ጥረት። በቡድን አስቢ የተባለች ግለሰብ፤ ነፃ ግለሰብ አይደለችም። አንድ ግለሰብ፤ መብቱ ከምን እንደሚመነጭ፣ ይዘቱ ምን እንደሆነና ወሰኑ የትላይ እንደሆነ ተገንዝቦ፤ የራሱ ውሳኔ መሥጠት ካልቻለ፤ የመሰሪ ፖለቲካ ልሂቃን መጫወቻ ጠጠር እንደሚሆን ግልጥ ነው። ይህ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የማያጠያይቅ ሀቅ ነው። ይሄ ካልተረጋገጠ፤ የግለሰብ መብት የለም ማለት ነው። በርግጥ የግለሰብ መብት በታሪካዊ ቦታውና በነባሩ ሁኔታ ይመነዘራል። ባሁን ሰዓት ደግሞ፤ አንድ ግለሰብ ራሱን ችሎ ኢትዮጵያዊ መሆኑ፤ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ፤ በአገሩ በማንኛውም ቦታ የመኖርና በሚኖርበት አካባቢ ኅብረተሰባዊ ክንውን የመሳተፍ መብቱ መከበሩ ነው። ይህ እንዲሁ በምኞት ወይንም መንግሥት ይሠጠኛል ብሎ በመጠበቅ የሚገኝ አይደለም። በተፈጥሮ የተሠጠን ጸጋም አይደለም። ለዚህ ለሁላችን የሚጠቅምና አብረን እንድንኖር የሚረዳን ሀቅ፤ ሁላችን በትክክል መታገል ይገባናል። ይህ መብት ቋሚ ከሆኑት መሠረታዊ ኢትዮጵያዊነት ጋር አምድ ሆኖ ሊሰለፍ ግድ ይላል። በትሕነግ ዘመን የተጋገረው የብሔርና ብሔረሰብ ግንዛቤ፤ አእምሯችንን ቆልፎ፤ ይሄን የግለሰብ ማንነት ግንዛቤ ሊያፈሰው አይገባም።

ይህ የቡድን እሳቤ ደግሞ፤ ራስን መቦደን ብቻ ሳይሆን፤ ሌሎች ከኛ የተለዩ ናቸው የሚል ትርክት በውስጡ አለው። የአገራችን የሚለው ጠፍቶ፤ የራሳችን ታሪክ፣ የራሳችን ባህል፣ የራሳችን እንጀራና ወጥ ይወጠወጥበታል! እናም ከዚያ፤ እኛና ሌሎች የሚለው፤ ወዳጅና ጠላት ወደሚለው ለመሻገር ድይድይ ዘርጉልኝ አይልም። ምክንያቱም፤ የኛ ያልሆነ እኛን የሚጎዳ ነው! የሚል መርዝ በውስጡ አለበትና! መጡብህ! መጡብሽ! የዚህ ርዕዩት ልሂቃን የሰበካ ቃጭል ይሆናል። ይህ የፖለቲካ ርዕዩት፤ የመኖርና አለመኖር ጥያቄ ይሆናል። ይሄንን አጥብቀው የተቀበሉና በዚህ የሰከሩ፤ በጣም ጽንፈኛ በመሆን፤ ከሰብዓዊነታቸው ወጥተው፤ የአውሬ ማንነት ይወርሳሉ። ይህን ነው ያየነው! በርግጥ ይህን የመለወጡ ሂደት አዝጋሚና አድካሚ ነው። መደረግ ግን የግድ አለበት። ይህ ሃይማኖት አይደለም፤ አልለቅም የሚለውን በአዲሱ ሕግ መጠየቅ ይቻላል። በነገራችን ላይ፤ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሃይማኖቶች፤ ጎረቤትህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው መልዕክታቸው። ይህ ከአውሬነት ያድናል።

በዚህ የአገራችን የፖለቲካ ሂደት፤ በትሕነግ በመመራት፤ ጠባብ ልሂቃን፤ ለራሳቸው የሥልጣን ጥማት ሲሉ፤ ራሳቸው ቀድመው ለዚህ እንደሚሞቱ ውሸት በመስበክ፤ ሕዝቡን ከሰብዓዊነት አውጥተው አውሬ አደረጉት። “እኛ ትክክለኞች!” “ሌሎች ሁሉ ስህተተኞች!” መለያ አጥሩ ሆነ። እኛ የምንኖረው ሌሎች ሲጠፉ ነው! የሚል የጨለማ ግንዛቤ አላበሱት። የዚህ ዓይነት ሰበካ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ማወቁ፤ የመጠቀ ትምህርትን አይጠይቅም። ይሄው አደጋውን አይተናል። ይህም ነው መግለጽ የሚያስቸግረውን አረመኔነት በአገራችን እንዲከሰት ያደረገው። የተደረገውን ደግሞ እዚህ ላይ የመግለጽ ፍላጎትም ሆነ ችሎታው የለኝም። ቁም ነገሩ፤ ይሄንን የቡድን ኢትዮጵያዊነት ሰርዞ፤ እያንዳንዱ ግለሰብ በራሱ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ማስመር ነው፡፡ ( ክፍል ፪ ይቀጥላል )

# ጉዞ ወደ ነገዋ ኢትዮጵያ (ክፍል ፪)

አንዱ ዓለም ተፈራ   ሰኞ ታኅሳስ ፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ. ም. (21/12/2020)

ቀጥለን ደግሞ፤ ትሕነግ ይሄን የአንድ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ አለመኖርና የቡድን ኢትዮጵያዊነትን ለመጋገር በሕገ–መንግሥቱ የዘረጋውን የአስተዳደር መዋቅር እንመርምር። ከዚህ በፊት ይህ ጸሐፊ፤ ባጋጠመው መድረክ ሁሉ በተደጋጋሚ እንደገለጠው፤ የአስተዳደር መዋቅር የሚዘረጋው፤ ለአስተዳደር አመቺ እንዲሆን ብቻ ነው። ሌላ ተግባር ሊኖረው አይገባም። በዚህ ጸሐፊ ዕድሜ፤ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን፤ ባሌ ከሐረር ተቆርሶ ክፍለ አገር ሆኗል። ከሌሎች ክፍለ አገራት ቦታዎች ተቆርሰው ወደ ሸዋ ክፍለ አገር ተመድበዋል። ሌሎች ተመሳሳይ ማሸጋሸጎችም በሌሎች ክፍለ አገራት ተደርገዋል። በአረመኔው የመንግሥቱ ኃይለማርያም ጊዜም የነበሩት ክፍለ አገሮች ተሰርዘው ሌላ መዋቅር ተዘርግቷል። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር ያዋቀረውን ልዩ የሚያደርገው ዋና ጉዳይ አለ። ከአነሳሱ ትግራይን ለይቶ ነፃ ለማውጣት ነበርና፤ አዲስ አበባ ገብቶም ይሄንን ዓለማውን አልቀየረም። ይህ መሠረታዊ እምነቱ፤ በምንም ደረጃ ላይ ቢቀመጥ የሚለወጥ አልሆነም። ስለዚህ፤ ማንኛውም ክንውኑ ያካሄደው፤ ይሄን ምኞቱን እንዲያሳካለት ነበር። ሕገ–መንግሥቱም ዓላማው፤ ሌሎች ነፃ የሚወጡ መንግሥታትን ማዘጋጀት ነበር። የአገራችንን ሙሉ ሥልጣን ይዞ፣ ሀብቷን ያለ ማንም ጠያቂ እንደግል ንብረቱ እየቸረቸረ፣ አገሪቱን እንዳሻው እየቆራረሰና እየፈነጨባት፤ እኔ ትግሬ ነኝ፤ እናንተም አማራ፣ ኦሮሞ፣ ደቡብ፣ ሶማሊ፣ አፋር፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ ናችሁ! እንጂ፤ እኔ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት አትችሉም! አለ።

ከላይ እንደጠቀስኩት፤ ይሄንን እንዲያሳካለት፤ በሕገ–መንግሥቱ አስፍሮ፤ ክልሎች የሚል መዋቅር ዘረጋ። እያንዳንዱን ክልል የየራሱ ሰንደቅ ዓላማ አስታቀፈው። ለያንዳንዱ ክልል የየራሱ መሥርያ ቋንቋ ሠጠው። እያንዳንዱ ክልል የየራሱ ልዩ ኃይል እንዲመሠርት አደረገ። የዚህ ሁሉ ድምር አሁንም በድጋሚ የተበጣጠሰች ኢትዮጵያን ማዘጋጀት ነበር። አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብትሆንም፤ ለሁሉም ወሳኝ ነገሮች ተጠሪዎ መቀለ ሆነች። ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶችም ወደ መቀለ እንዲያተኩሩ ተደረገ። ከሞላ ጎደል ትግራይ ራሷን የቻለች ሌላ አገር ሆነች። ማንም የትግራይ ተወላጅ ያልሆነ፤ ትግራይ ውስጥ ባዕድ ሆነ። ይህ ደግሞ በኦሮምያ፣ በደቡብ፣ በሶማሌና በሌሎችም ተተግብሯል። በዚሁ ሕገ-መንግሥት፤ ኦሮሞው ከሶማሊው፣ አማራው ከኦሮሞው፣ የሚገርመው ደግሞ በደቡብ ክልል ያሉት አንዱ ከሌላው ጋር ርስ በርሳቸው እንዲጋጩ ተሠራበት።

ለዚህ እንግዲህ መፍትሔ የሚሆነው፤ ከምርጫው በፊት ከትሕነግ ፍልስፍናና አሰራር የተለየ መዋቅር መዘርጋት ነው። ይህ መዋቅር፤ መሠረታዊ የሆነውን የአወቃቀር ሂደት መከተል አለበት። አሁን በአገራችን መንግሥት አለ። እንደ መንግሥትነቱ ደግሞ ኃላፊነት አለበት። ትክክለኛ የሚሆነው፤ ታዋቂ ግለሰቦችን፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከተደራጁ ክፍሎችና ከብልፅግና የተውጣጣ የስግግር መንግሥት ሰይሞ፤ እኒህን ቅድመ ሁኔታው የሚጠይቃቸው ክንውኖች ማስቀደም፤ ዘላቂ ሰላምን በአገራችን ያሰፍናል። እናም ይህ አካል መዋቅሩን ቢዘረጋው ጥሩ ነው። የአስተዳደር መዋቅር አንድና አንድ ዓላማ ብቻ ነው ሊኖረው የሚገባ። የአስተዳደር መዋቅር የአንድ ፓርቲ የፖለቲካ ግብ መምቻ ሊሆን አይገባም። ይህ የአገርና የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ውሳኔ መሆን አለበት። ቋሚ በሆነ መንገድና በአንድ ፓርቲ ሳይሆን በመላ ሕዝቡ ተወካዮች ሊተገበር የሚገባው ጉዳይ ነው። ለአስተዳደር አመቺነት ብቻ ነው መመዘኛው የሚሆነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውንም ኅብረተሰባዊ ክንውን በኢትዮጵያዊነታችን እንሳተፍ ካልን፣ በየትኛውም የአገራችን ቦታ በኢትዮጵያዊነታችን በሙሉ መብት መሳተፍ አለብን ካልን፣ ሁሉም የአገራችን ቦታ የኔ ነው ካልን፣  አንዱን የአገራችን ክፍል ከሌላው ለይተን የማናይ ከሆን፤ ዛሬ የአንዱ ክልል፣ ነገ ደግሞ በሥራ ምክንያት ወይንም በንግድ ጉዳይ የሌላው የአገራችን ክፍለ አገር ባለቤት መሆን አለብኝ ካልን፣ በዚህ ጸሐፊ እምነት፤ የአስተዳደር መዋቅሩ መመዘኛ ሊሆኑ የሚገባቸው የሚከተሉት ናቸው። አንደኛው የሕዝቡ ቁጥር ነው። ቀጥሎ ደግሞ ኩታ ገጠምነት ነው። ለዚህ የተፈጥሮ ከለላዎች ይረዳሉ። ከዚያ የገበያ አመቺነት ነው። ቀጥሎ የሕዝብን እንቅስቃሴ ረዳትነቱ ነው። በተቃራኒው፤ ቋንቋ፣

ታሪክ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ በምንም መንገድ ከመመዘኛነት ሊቆጠሩ አይገባም። ቋሚ የአንድ ክፍለ አገር ብቻ ነዋሪነት ጎጂ ነው። ለምን ቢባል፤ ይሄ አስተሳሰብና እምነት፤ አሁን ላጋጠመን ሂደት ማሳያ ነውና!

በመፍትሔ በኩል፤ ለመንደርደሪያ ያህል የሚከተለው ይስፈር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር አንድ መቶ አስር ሚሊዮን ነው የሚለውን መነሻ እናድርግ። ይህ በቀጥታ አገራችንን በአስር ሚሊዮን ሕዝብ የተደለደሉ ክፍለ አገራት እንዲዋቀሩ ይረዳል። ተከትሎ ደግሞ ይህን አስር ሚሊዮን ሕዝብ፤ አንድ አንድ ሚሊዮን ያላቸው የክፍለ አገር ክፍሎች (አውራጃዎች ማለት ይቻላል) ማቋቋም ያስኬዳል። ይህ ደግሞ በተራው፤ አንድ አንድ መቶ ሺ ሕዝብ ያላቸው ወረዳዎችን ይጠራል። እንግዲህ እነኚህ ወረዳዎች ከላይ በተጠቆመው በአስተዳደር አመቺነታቸው ይዋቀራሉ። የሕዝቡ እንቅስቃሴ፣ የገበያ አመቺነት፣ ኩታ ገጠምነቱና የተፈጥሮ ለክልል አመቺነት ተመዝኖ ሊካሄድ ይገባል። ይህ መንደርደሪያ ሆኖ፤ ከኔ የበለጠ የአስተዳደር ዕውቀቱና ልምዱ ያላቸው ቢመለከቱት ጥሩ ነው። ለዕኩልነትና ለትክክለኛ አገራዊ አስተዳደር አመቺነቱን ልብ ይሏል።

እንግዲህ ለናሙና፤ የግለሰብ ማንነትና የአገር አስተዳደር መዋቅሩን ዓይተናል። እነኚህ ሳይለወጡ የሕዝቡ ትግል ግቡን መትቷል ማለት አይቻልም። ይሄን ሳናረጋግጥ ወደፊት ግስገሳና ወደ ምርጫ ሩጫ፤ አደባብሰው ቢያርሱ . . . ነው። በርግጥ ይሄንን በተዓምር እንዲሆን ባለንበት ተቀምጠን መጠበቁ ከየዋኅነት ያለፈ ትርጉም የለውም። መገንዘብ ያለብን፤ የአገር የፖለቲካ ሂደት፤ በአንድ ግለሰብ ወይንም በአንድ ቡድን ቀናነትና ፍላጎት አይገነባም። የአንድ ግለሰብ በጎ መሆን፤ የመንደሩን በጎነት አያበስርም። አንድ ፓርቲ ጥሩ መሥራቱ፤ በአገሪቱ ብቻውን እስሆነ ድረስ፤ አገሪቱ ዴሞክራሲያዊት ናት አያሰኝም። ይልቁንም አንድ ፓርቲ ብቻውን መኖሩ፤ በአገሪቱ አምባገነን መንግሥት እንዳለ አብሳሪ ነው። ታዲያ ምን ይደረግ?

በአገራችን ያለው ትልቁ መሠረታዊ ችግር፤ አማራጮች መኖራቸው እንዳስፈላጊ ሳይሆን እንደ አደጋ መታየታቸው ነው። በዕለት ተዕለት ተግባራችን ብዙ ምርጫዎች ኖረውን፤ ሁሉንም እንዳስፈላጊነታቸው ደርድረን፤ የወደድናቸውን ይዘንና ሌሎችን ጥለን፤ ቅደም ተከተል በማበጀት ወደፊት እንሄዳለን። በአንድ አገር ውስጥ የተለያዩ ፓርቲዎች ተቃዋሚዎች የሉም። ያሉት ተፎካካሪዎች ናቸው። ተፎካካሪዎች መኖራቸው ደግሞ ሁሉንም ጥሩ እንዲሆኑ ይረዳል። እናም ተፎካካሪ ሊወደድና ሊከበር የሚገባው ነው። ፖለቲካው ይሄን ወለሉ አድርጎ ሊወስደው ይገባል። በነገራችን ላይ፤ ይህ ጉድለት በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በተፎካካሪ ድርጅቶችም ውስጥ ያለ የአመለካከት ጉድለት ነው። ራሳቸውን እንደ ተፎካካሪ ሳይሆን እንደ ተቃዋሚ አድርጎ መውሰድ።

አብዛኛውን ጊዜ የተፎካካሪ ድርጅቶችን የትግል ሂደት መመልከቱ ጨለማ ውስጥ ይከታል። በውጪ አገራት፤ በአውሮፓና በአሜሪካ፤ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን ይዘን ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግና የአቤቱታ ፊርማዎችን ማሰባሰብ ዋና የትግል መስመራችን ሆኖ ለረጅም ጊዜ አገልግሏል። ለዚያውም የድርጅቶቻችንን አባላት ሳይሆን ፈቃደኛ የሆኑ አገር ወዳዶችን በማሰባሰብ! ድርጅቶቹ የሚፈልጉትን ማወቅ፣ ከገዥው ፓርቲ ያላቸውን የፖለቲካ ልዩነት መረዳት፣ የውስጥ አሠራራቸውን መለየት፣ የሂደታቸውን ቅደም ተከተል መገንዘብ፤ በጣም አስቸጋሪ ነው። አብዛኛውን ጊዜ፤ ለትናንት ነው ወይስ ለዛሬ፣ ለነገ ነው ወይንስ በጭንቅላታቸው ውስጥ ለፈጠሩት ወቅት የሚታገሉት! ያስብላል። ለየትኛው እውነታ ነው የሚታገሉት? መቸም ያለውን ሥርዓት የሚተካ ሌላ አማራጭ ሳይይዙ፤ ያንን ሥርዓት መቃወምና የዚያኑ ሥርዓት መልዕክትና ግብ ይዞ መፎካከር አይቻልም። ትልቁ የተፎካካሪዎች ችግር ደግሞ፤ የተለያየ ፍላጎትና ግብ ያነገቱ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ ወደ አንድ መሐከል የሚያመጣቸውን አማካይ ፈልጎ፤ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አብረው እንዲሠሩ ርቆ የሚያስብና የሚያስተባብር መሪ አለማግኘታቸው ነው። እናም በጋራ ፍላጎታቸው ዙሪያ ለመሰብሰብ አለመቻላቸው ነው። ይህን ያለው መንግሥትም ሆነ ሌላ አካል ሊያደርግላቸው አይችልም። ራሳቸው ማድረግ አለባቸው።

እዚህ ላይ ለማጠቃለል፤ ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! እያልን አሁን በአገራችን የሰፈነውን የብሔር ብሔሮች አገዛዝ መደገፍ አይቻልም። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ የትሕነግ የፖለቲካ ፍልስፍናና የአስተዳደር ቀመር፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከሥሩ መንግሎ የሚነቅል መርዝ ነው። ያንን አሁንም ይዘን ወደፊት እንቀጥል ማለቱ፤ አንድም ለነበረው ሥርዓት አሁንም ማጎብደድ ነው፤ አለዚያም በትክክል አገር እንድትፈርስ ተግቶ መሥራት ነው። አልፎ ተርፎ ደግሞ፤ ለውጡ እንዲመጣ ውድ ሕይወታቸውን የገበሩትን ሀቀኛ ኢትዮጵያዊያን ዋጋ ማሣጣት ነው። ታዲያ አሁን አገራችን በየትኛው ጎዳና እየተጓዘች ነው!

በሕዝቡ በኩል ባለሥልጣናትንና ልሂቃንን ሙሉ በሙሉ የመቀበልና ያሉትን የማምለክ ዝንባሌ ይታያል። የሚናገሩትን መፈተሽ አልተለመደም። ባለሥልጣናትን መጠየቅ አደጋ የሚያስከትል ሆኖ በታሪክና በደንባችን ተጋግሯል። የግለሰብን ኢትዮጵያዊ ማንነት ማረጋገጫ ምንም ዓይነት መንገድ አልተዘረጋም። ሲሾም ያልበላ ይባል የለ!

ባሁኑ ሰዓት የብልፅግና ፓርቲ፤ ከፌዴራል መንግሥቱ አንስቶ እስከ የመንደር ቀበሌና የገበሬ ማህበራት ድረስ መላ አገሪቱን ተቆጣጥሯል። ለይስሙላ እዚህም እዚያም እንደ ነጥብ ተንጠባጥበው የሚገኙ ተፎካካሪ ድርጅቶች፤ በአብዛኛው አዲስ አበባ የሰፈሩ ናቸው። አሁን በሚደረገው ምርጫ፤ ብልፅግና ፓርቲ መቶ በመቶ በሚባል ደረጃ በአቸናፊነት ይወጣል። ይህ ዴሞክራሲ አለመኖሩን ከማረጋገጥ ሌላ፤ ምንም ትርጉም አይኖረውም። ለምን ቢባል፤ መደረግ የነበረባቸው ጉዳዮች፤ ለብልፅግና ማቸነፍ ሲባል ተዘለዋልና! በድጋሜ ላንሳውና፤ የሕዝብ ቆጠራ መደረግ አለበት። ሕገ-መንግሥቱ መለወጥ አለበት። አገሪቱን በአዲስ መካለልና፤ በነዚህ አዳዲስ ክፍለ አገራት የሚኖሩ አባላት ናቸው የየራሳቸውን ወኪሎች መምረጥና መላክ ያለባቸው። ይህ ሂደት፤ ብልፅግናን እንዳያቸንፍ ያደርጋል ማለት አይደለም! ብልፅግና ዕውቅናን ሊያገኝ የሚችለው፤ ብልፅግናን በበቂ ሊወዳደረው የሚችል ሌላ ድርጅት ወይንም ድርጅቶች ሲኖሩ ነው። ያንን ማድረግ ደግሞ የራሱ የሆነ ግዴታ አለበት። ብቁ ተወዳዳሪ በሌለበት ሜዳ ብቻውን ተወዳድሮ አቸነፍኩ ቢል፤ ትርፉ ዘበትና አምባገነንነት ነው።

የትሕነግ ርዕዩተ ዓለም መሠረት የሆኑት መፍረስ አለባቸው። በዚያ ላይ ነው አዲሱ ሥርዓት የሚገነባው። በትሕነግ አልጋ ተኝቶ ሌላ ሳይሆን የትሕነግን ሕልም ነው ማየት የሚቻለው። ይዘቱን ሳይቀይሩ እንሂድ ማለት፤ ጉልቻውን ቀይሮ ወጡ እንዲጣፍጥ መጠበቅ ነው። ሕዝብን ማዳመጥ ያስፈልጋል። አንድ ግለሰብ በየትኛውም የኢትዮጵያ መሬት በትሕነግ ተፈነቀለ ካልን፤ ይህ ግለሰብ ወደ ቦታው መመለስና ካሣ መቀበሉ ቅድመ ሁኔታ ነው እንጂ፤ መቀመጫውን ላጣ ግለሰብ፤ ሌሎች ቅድመ ሁኔታ ሆነው፤ ይህን በሁለተኛ ደረጃ ማስቀመጡ ወደፊት አያስኬድም።

eske.meche@yahoo.com